“ አስነዋሪው“ የዶክተር ነገደ መፅሃፍ

# የምን ሴራ አቶ በረከት? ቦምብ ነው እንጂ!!!

የካቲት ሃያ ቀን በኢህአዴግ ተወካዮችና በተቃዋሚዎች መካከል የተደረገውን ክርክር ሳዳምጥ በአቶ በረከት ስምኦን አጋፋሪነት የዶክተር ነገደ መፅሃፍ ዋና የመነጋገሪያ ነጥብ ሆኖ ሳየው መጀመሪያ የመጣብኝ ሃሳብ ምናልባት ሰ ው ሁሉ ያሰበው ነገር ነበር። አቶ በረከት ትንሽ ጆርጃሪ ብጤ ስለሆኑ ለዚህ መፅሃፍ ገንዘብ የማይገዛው ማስተዋወቂያ እያደረጉ ነው፤ እንደተለመደው ብልጣ ብልጡ አቶ መለስ በዚህ አፍ እላፊ ይቆጧቸውና ፋይሉ በዚሁ ይዘጋል ብየ አ ስቤ ነበር። ነገሩ መልሶ ቀልሶ ወልደ አረጋይ ለቅሶ ሆነ። “በሴረኛውና በስልት መሃንዲሱ“ ዶክተር ነገደና በመፅሃፋቸ ው ላይ ቅስቀሳው ተጧጧፈ። ከብርክ የሚዋሰነውን የፕሮፓጋንዳ ውርጅብኝ ስታዘብ ከዚህ ጆርባ ብልጣ ብልጡ አቶ መለስም አሉበት የሚለው መደምደሚያ ላይ ደረስኩ። ድርጅታዊ ስትራቴጂ ነው አልኩ። መፅሃፉ አገር ውስጥ እስኪ ታተም መጠበቅ አልቻልኩም። ፎቶ ኮፒ እየተደረገ ውስጥ ውስጡን ከሚሰራጨው አንዲት ቅጅ 75 ብር ገዝቼ አነበ ብኩት።

እንዲህ የተጣደፉኩት በዚህ መፅሃፍ የሆነ ”ሴራ” አገኝበታለሁ ብየ አይደለም። እርግጥ በቴሌቪዥን እንደታየ ው የአቶ በረከት ”እደነፋፋት” ነገሩን እጅግ ውስብስብና ረቂቅ በሆነ የመረጃ መረብ ”የደረሱበት” ያስመስላቸው ነበ ር። በመኢሶን አባላት መሃል ውስጥ ውስጡን በጥብቅ ምስጢር የሚሰራጭ ወይም ለተወሰኑ የህብረቱ መሪዎች የተላከ የዶክተሩ ፊርማ ያለበት ምስጢር ሰነድ ስጠብቅ ሰውየው የሴራው ማስረጃ ብለው በይፋ ታትሞ የወጣና የተሰራጨ መፅሃፍ እያውለበለቡ ለኤግዚቢት አቀረቡና ቁጭ አሉ። በይፋ የሚካሄድ አዲስ አይነት ሴራ መሆኑ ነው ማለት ነው። የመፅሃፉ ይዘት ”አስነዋሪ” ነው የተባለውን ክስ ድሮም ቢሆን ከዶክተር ነገደ (ያውም በዚህ እድሜያቸው) ድርሳነ ወ ሲብ (ፖርኖግራፊ) ስለማልጠብቅ ከቁም ነገርም አልጣፍኩት ነበር። ይፋ ከሆነ ምኑን ሴራ ሆነው? ሴራ ከሆነ ለምን በ ራሳቸው ”በሴረኛው” ይፋ ተደረገ? ከምትለው ቀላል ስሌት ተነስቼ የሴራውንም ውንጀላ ለማሰናበት ብዙም ጊዜ አልወ ሰደብኝ። ጥያቄው የመስመርና የፖለቲካ ትግል ስትራቴጂ ጉዳይ መሆን አለበት በሚል እምነት መፅሃፉን ተያያዝኩት ።

አቶ በረከት ይኸ ”ይፋ ሴራ” የህገ መንግስቱን ስርአት ብሎም አገር ”በማፍረስ” ላይ ያነጣጠረ መሆኑን ጠቆ ም ያደርጋሉ። እርግጥ አገራችን አመድ በዱቄት የሚስቅበት አስገራሚ ዘመን ውስጥ ከገባች ትንሽ ሰንብታለች። ይህ ንን እያወቅሁም ቢሆን ያውም አቶ በረከትን የመሰለ ሰው ያውም ዶክተር ነገደን የመሰለ ዜጋ ”በሃገር ማፍረስ ሴራ” ሲ ወነጅሉ ስሰማ ከዚች አገር ይሉኝታ የሚሉ ነገርም እየጠፋ ነው ብየ አዘንኩ። የሆነ ሆኖ አቶ በረከት በዚህ በህገ መን ግስት ጉዳይ ብዙ አልገፉበትም። ዋናው መልእክታቸው ይኸ አይደለም። ”አጭበርብረን በምናሸንፈው ምርጫ ማግስ ት ተቃዋሚው ’ምርጫው ተጭበረበረ’ ብሎ አመፅ ለማስነሳት ከዶክተር ነገደ መመሪያ እንደደረሰው ደርሰንበታል። ዝ ም ብለን አናይም። ይህንን እንቅስቃሴ ለመደምሰስ በህጉ መሰረት እንንቀሳቀሳለን። ስለዚህ ከወዲሁ ተቃዋሚ ሁሉ ከ ዚህ አስነዋሪ መመሪያ/መፅሃፍ ራሱን ይነጥል። አለበለዚያ በሃገር ማፍረሱ ሴራ ተባባሪ መሆኑን ማወቅ አለበት” የሚል መልእክት ነው። ሆኖም ይህንን ትቼ ይበልጥ ወደ ከነከነኝ ጥያቄ ተመለስሁ። እዛው የምሽቱ ክርክር ላይ አንዳንድ ተከራካሪዎች ”ባይሆን እንደ አንቀፅ 39 አይነቱን የማሻሻል እንጂ እኛ ህገ መንግስታዊ ስርአት የመቀየር አላማ የለንም ” እያሉ ሲሟገቱ የኔም ሃሳብ እንደነሱው ስለነበረ ሁለት ጥያቄዎች መጡብኝ። ዶክተር ነገደ ከዚህ አንዳንድ አንቀፆ ችን ከማሻሻል ሃሳብ አልፈው ህገ መንግስታዊ ስርአት ይቀየር ይላሉ ወይ? ሁለተኛ ይህንን ካሉስ መቸም የህግ ተማሪ ናቸው ማለትን ሰምቻለሁና ይህንን አቋማቸውን እንዴት ነው የሚደግፉት?

አወን ደራሲው በግልፅ በይፋ ምንም በማያሻማ ሁኔታ ይህ ህገ መንግስታዊ ስርአት ”የሚሻሻል” አይደለም ተ ቀይሮ በሌላ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት ስርአት መተካት አለበት ይላሉ። ለምን? እንዴት? እያሉ ሲተነትኑ ሳነብ ገና

መፅሃፉን ሳላገባድድ ነው የዚች መጣጥፌ ርእስ የመጣልኝ። የምን ሴራ አቶ በረከት? የዶክተር ነገደ መፅሃፍ ቦንብ ነው።

በኔ ግምት ይህ "በአመፅ" ላይ ያተኮረ የኢህአዴግ ስትራቴጂ ዋና አላማው ሰው ሁሉ በዚህ "የምርጫ ማግስት ሴራ አለ ወይስ የለም?" በሚለው ክርክር ላይ እንዲረባረብ በማድረግ ይህንን በህገ መንግስቱ በኩል ያለውን ቦምብ ለማክሸፍ ይመስለኛል። ይህ ወያኔያዊ ስትራቴጂ ደግሞ እየሰራ ነው። አንዳንዱ ተቃዋሚ ከድንጉጥነትም ይሁን ከሌላ ከምን ነገር እንደሆን ሳይታወቅ "ራሳችሁን ለዩ" በሚለው የአቶ በረከት ማስፈራሪያ እየተሸነፈ ነው። በሌለ ሴራ ውስጥ "የለሁበትም" እያለ ለወያኔ ሴራ መመቻቸት ጀምሯል። አብዛኛው ተቃዋሚ፤ ነፃ ፕሬሱና ዴሞክራት ደግሞ ለወያኔ ፕሮፖጋንዳ እየሰጠ ያለው የመልስ ምት " የለም ዶክተሩ አላሴሩም " የሚል በምርጫ ሂደትና ውጤት መፅሃፉ የሚለውን በማብራራት ላይ የተወሰነ መልስ ነው። ይህ አካሄድ የሚስተው አንድ ቁም ነገር አለ። የዚህ መፅሃፍ ትኩረት ደራሲው "ስታሊናዊ ህገ መንግስታዊ ስርአት" ብለው በሚጠሩት ጉዳይ ላይ ነው። ስለ "ሴራው" የሚደረገው ርብርቦሽ ደራሲው በዚህ በህገ መንግስት ጉዳይ በኢህአዴግ ስርአት ላይ የጠመዱትን "ሰላማዊ ቦንብ" እንዲድበሰበስ አድርጎታል።

እርግጥ መፅሃፉ ስለ ምርጫ ሂደትና ስትራቴጂ ብዙ ቁም ነገሮች አሉት። ይህም ሆኖ ዶክተር ነገደ ስለ ግንቦቱ ምርጫ ብዙም የሚጨነቁ አይመስልም። እንዲያውም በየአምስት አመት በፖለቲካው መድረክ ብቅ ጥልቅ በሚል ሂደት ብቻ ተማምነን የትም አንደርስም ባይ ናቸው። በዚህ ጉዳይ የደራሲው ፅኑ እምነት በኢህአዴግ ህገ መንግስታዊ ስርአት ስር እስካለን ድረስ በኢትዮጵያ መድበለ ፓርቲ ምርጫ ሊደረግ አይችልም የሚል ነው። ይህንንም በሰፊና አሳማኝ በሆነ ትንተና ያስረዳሉ። ቀጠል አድርገው ደግሞ በኢህአዴግ ህገ መንግስታዊ ስርአት ስር በሚደረጉ ምርጫዎች በሙሉ ልብ መሳተፍ አለብን ይላሉ። ችኩል አንባቢ ደራሲው በየመስመሩ ራሳቸውን በራሳቸው ይቃረናሉ የሚል መደምደሚያ ሳይደርስ ሰውየው ተሸቀዳድመው እንዴት? ለምን? በምን አላማ መሳተፍ እንዳብን አሁንም ቢያንስ ለኔ አሳማኝ በሆነ አቀራረብ ያስረዳሉ። አቋማቸውን ጠቅለል አርገው ሲያቀርቡ፤

"በዚህ መድበለ ፓርቲ ምርጫን በማይፈቅድ ህገ መንግስታዊ ስርአት ስር ዛሬም ሆነ ነገ በምርጫ ሂደት የምንሳተፈው <u>*መድበለ ፓርቲ ምርጫ የሚቻልበት ስርአት ለማምጣት በተለያዩ ሰላማዊ ስልቶች የሚደረገውን ትግል ለማገዝ ነው"*</u>(ገፅ 154 ስርዝ የሳቸው ነው።)

ለማንኛውም ይህንን የምርጫ ስትራቴጂ ጉዳይ ያነሳሁት በቅጡ ወደ ህገ መንግስቱ ጥያቄ ለመግባት ነው። የዶክተር ነገደ ዋናው ጭንቀት ህገ መንግስታዊው ስርአት ነው። የዛሬ ሁለት ወሩ የግንቦቱ ቀርቶ 'በኢህአዴግ ህገ መንግስታዊ ስርአት እስካለን ድረስ' የም-ርጫ ሚና ወደ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስታዊ ስርአት የሚደረገውን ሰላማዊ ህዝባዊ ትግል ለማገዝ እንደሆነ ደግመው ደጋግመው ያስምሩበታል። ደራሲው ህገ መንግስታዊ ስርአት ለውጥ ሲሉ የአክራሪነት አባዜ ይዟቸው ነው ወይስ አሳማኝ ምክንያት አላቸው? እንግዲህ ወደ ህገመንግስታዊው 'ቦንብ' ልግባ። መጀመሪያ በዚህ ጉዳይ ኢህአዴግ ስለተሰማራበት ከሸብር ፈጠራ የሚዋሰን ፕሮፖጋንዳ አንዳንድ "ኤሌሜንታሪ" ሃቆች ላቅርብ። ከዚያ ደራሲው ህገ መንግስቱ ይቀየር የሚሉት ለምንድን ነው? ለዚህስ መደረግ ያለበት ትግል እንዴት ይካሄድ ወደሚሉት ነጥቦች እገባለሁ።

1ኛ. ህገ መንግስት ማሻሻል፤ መቀየር ወይስ ስርአት ማፍረስ?

አቶ በረከት ዶክተር ነገደ ህገ መንግስታዊው ስርአት "መፍረስ" አለበት በሚል ሰበብ "አገር ለማፍረስ" የሚንቀሳቀሱ ሴረኛ ናቸው ይሉናል። ይኸ እንግዲህ የአበየን እከክ ወደ እምየ ለከክ እንደተባለው መሆኑ ነው። በጤናማ አካሄድ የህገ መንግስታዊ ስርአት "መፍረስ" ከሃገር "መፍረስ" ጋር አይያያዝም። በወያኔዊ አካሄድ ደግሞ ከህገ መንግስት ስርአት መቀየር ጋር አገርም ሲፈርስ ታይቷል። የዶክተር ነገደ አካሄድ ግን አገራችንን ዴሞክራሲያዊት እናድርጋት የሚል እንጂ በእንዲህ አይነቱ አፍራሽነት ሊጠረጠር የሚችል አካሄድ አይደለም። "ማፍረስ" የሚለው "አፍራሽ" ቃ

ል በመፅሃፋቸው አንድም ቦታ የለም። ለነ አቶ በረከትና አሁን እንደምናየው ደግሞ ለአንዳንድ "እኛ ስር ነቀል ለውጥ አንደግፍም" በማለት የዶክተር ነገደን አቋም ለማጥላላት ለተነሱ ድንጉጥ ተቃዋሚዎች ለመፅሃፉ "አፍራሽነት" ተገኘ የተባለው "መረጃ" ምንድን ነው? ለዚህ ያገኘሁት ፍንጭ ደራሲው ህገ መንግስቱን "ማሻሻል" የሚለውን ሃሳብ በግልፅ መቃወማቸው ነው።

" በተቃዋሚው ጎራ አንዳንዶች ስለ ህገ መንግስቱ መሻሻል ሲያወሩ ከአጠቃላይ የዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት መርህዎች አንፃር ሳይሆን ከራሳቸው ፖሊሲና ወገናዊ የፖለቲካ ፕሮግራም ተነስተው እንደሆነ እየታዘብን ነው። 'ትግላቸው' ከሰነዱ ውስጥ 'የማይስማሙባቸውን' እንደ አንቀፅ 39 እና 40 አይነቶቹን አንቀፆች መዝዞ 'በማሻሻል' ላይ ያተኮረ ግንጥል ትግል ይመስላል። ይህ ህገ መንግስት ግን አንቀፅ በአንቀፅ የሚሻሻል ሳይሆን እንዳለ ከነፍልስፍናው መቀየርና በሌላ መተካት ያለበት ሰነድ ነው" በማለት "ማሻሻል" የሚለውን ቃል ያጣጥሉታል። (ገፅ 162)

ለሳቸው ዋናው ቁምነገር ከስታሊናዊው ህገ መንግስታዊ ስርአት ወደ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስታዊ ስርአት መሸጋገሩ ነው። አንዳንድ አንቀፆችን መዞ በማሻሻል ይህንን ህገ መንግስታዊ ግብ እንመታለን የሚሉ ወገኖች ካሉ ደራሲው እዚህ "ማሻሻል" ወይስ "መቀየር" የሚለው ፀጉር ፈለጣ ውስጥ አይገቡም።

" የግድ አንድ አንቀፅ ይመዘዝና ይሻሻል ከተባለ ደግሞ ዴሞክራሲ፤ የህግ የበላይነት፤ የዳኝነት ነፃነት ወዘተ... እስካልን ድረስ ከአንቀፅ 39 ይልቅ የህገ መንግስቱ የማእዘን ዲንጋይ በሆነው በአንቀፅ 50/3 ላይ ማተኮር ያስፈልጋል እንላለን። አንቀፅ 50 ሳይነካ የአንቀፅ 39 መሻር ብቻውን ይህንን ህገ መንግስት ዴሞክራሲያዊ አያደርገውም።"(ገፅ 162) ደራሲው ይህንን ሲሉ ስለ "ህገ መንግስት ማሻሻልና" ስለ ህገ መንግስታዊ ስርአት መቀየር ጉዳይ ካላቸው አቋም እያፈገፈጉ አይደለም። "የማእዘን ዲንጋዩ" ከተነሳ፤ የኢህአዴግ ህገ መንግስት የተገነባበት ስታሊናዊ የህገ መንግስት ቲዎሪ "ፈረሰ" ማለት ነው። እኔ እንደተረዳሁት ከሆነ ይህ አንቀፅ 'ተሻሽሎ' በስልጣን ክፍፍል መርህ ሲተካ 'ማንም ሳይነካቸው' ተያይዘው የሚነጉዱ ሃያም ሰላሳም አንቀፆች ይኖራሉ።

መፅሃፉ ዋሽንግተን ለንባብ እንደበቃ በአካባቢው የሚታተም "ዘ ኢትዮጵያ" የተባለ ጋዜጣ "ዶክተር ነገደ አዲስ መፅሃፍ ፃፉ - ከአንቀፅ 39 አንቀፅ 50 ይብሳል ይላሉ!" በሚል ርእስ ተነስቶ ሰፊ ሃተታ ማቅረቡን ሰምቻለሁ። በዚህ አንቀፅ ላይ የዶክተር ነገደ ውርጅብኝ ከየት መጣ? እንግዲህ ወደ ኢህአዴግ ህገ መንግስት ይዘት እንሂድ።

2ኛ. ህገ መንግስታዊ ስርአትን መቀየር አስፈላጊነት

ዶክተር ነገደ በዚህ ጉዳይ የኢህአዴግን ህገ መንግስት "ስታሊናዊና አደገኛ" ብለው በሰልሳ ገፅ ገምግመውታል። የዛሬ ስንት አመት እንደሆነ ትዝ አይለኝም እንጅ ለአንድ ለሆነ ጋዜጣ በሰጡት ቃለ ምልልስ "የዚህን ህገ መንግስት ይዘት ሳይ በፈረንሳይ ሃገር ህግ ፋኩልቲ ስማር *"የስታሊናዊ ህገ መንግስት - በቲወሪና በተግባር"* በሚል ርእስ የወሰድኩት ኮርስ ከፊቴ ተደቀነ።" በማለት የተናገሩት ትዝ አለኝ። እዚሁ መፅሃፋቸው ላይ ደግሞ ሰነዱን "በህገ መንግስት ባለሙያዎች አካባቢ ልክ እንደ ደርጉ ዘመን (ይህ የኢህአዴግም ሰነድ) ለስታሊናዊ ህገ መንግስት ቲወሪና አሰራር በናሙናነት ሊቀርብ የሚችል ሰነድ" በማለት ነገሩን "ጠቅለል" አድርገው ካቀረቡ በኋላ ወደ ዝርዝር ትንተና ይገባሉ። እዚህ ዝርዝር ውስጥ እምብዛም አልገባም።

ባጭሩ ግን የሚሉት ምንድን ነው? የዛሬው የኢህአዴግ ህገ መንግስት በወሳኝ መልኩ የደርግ ህገ መንግስት ፎቶ ኮፒ ነው። የዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት የማእዘን ዲንጋይ የስልጣን ክፍፍል መርህ የሆነውን ያህል የደርግም የኢህአዴግም ህገ መንግስት የማእዘን ድንጋይ የስልጣን አንድ ወጥነት የሚለው ስታሊናዊ ቲዎሪ ነው። ይህ የሚገለፀው ደግሞ በየትኛውም ስታሊናዊ ህገ መንግስት በሚደነገገው "ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን አካል" (Highest organ of state authority) በሚባለው *"ጭራቅ"* አማካኝነት ነው። የስራ ማስፈፀሙም፤ የዳኝነቱም፤ የህገ መንግስታዊ ቁጥጥሩም...ሁሉም ስልጣን በዚህ "የበላይ አካል" ቁጥጥር ስር ነው።

እንግዲህ በዚህ ጉዳይ መጀመሪያ መሰመር ያለበት ነገር አለ። ይኸ እንግዲህ ቦምብ ቁጥር አንድ መሆኑ ነው። በስልጣን ክፍፍል መርህ በሚሰሩ ዴሞክራሲያዊ አገሮች እንዲህ ያለ “የመንግስት ስልጣን ከፍተኛ አካል” የሚባል ነገር የለም። የዛሬ አስር አመት ሰነዱ ሲፀድቅ 18 ዴሞክራሲያዊ አገሮች ተጠሪዎች ዶክተር ነገደ እንዳሉት ”በሃገራችን የውስጥ ጉዳይ ሰርስረው በመግባት” ይህንን ሰነድ ዴሞክራሲያዊ ብለው አሞካሸተውት ነበር። ዛሬ ተቃዋሚ ሃይሎች ደራሲው በመፅሃፋቸው ያቀረቡትን መሰረታዊ ጥያቄ ለነዚህ ዴሞክራሲያዊ አገሮች ተወካዮች በይፋ ማቅረብ ይኖርባዋቸል። ለምሳሌ በአሜሪካ የትኛው የመንግስት ዘርፍ ነው ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን አካል? ፕሬዜዳንቱ? ኮንግረሱ? ወይስ ከፍተኛው ፍርድ ቤት? ዶክተር ነገደ በመፅሃፋቸው ይህንን ጥያቄ ሲያቀርቡ መልሱን አጥተውት አይደለም። እዛው አያይዘው ” የትኛቸውም አይደሉም” ብለው ይመልሳሉ። (ገፅ 100)

ሁለተኛ በየትኛውም ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስታት የሌለው ይህ ጭራቅ አካል ታዲያ የት የት ነበር? ዛሬስ የት የት ነው ያለው? የሚለው ጥያቄ ይነሳል። ይኸ ደግሞ ሁለተኛው ቦንብ መሆኑ ነው።

”ከታሪክ አንፃር” እንዲህ አይቱ ጭራቅ አካል የት የት ነበረ? በሶቭየት ህብረትና ”የኛን” ደርግ ጨምሮ የሷ ተቀጢሳ በነበሩ 'ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ' ሃገሮች -

“ የሶቭየት ህብረት ህገ መንግስት አንቀፅ 108 'በሶቭየት ህብረት የመንግስት ስልጣን ከፍተኛ አካል ሱፕሪም ሶቭየት ነው' ይላል። የእንዲህ አይነቱን አካል ከፍተኛነትና ከስልጣን ክፍፍል ይልቅ አንድ ወጥነትን በግልፅ የሚያስቀምጠው የቡልጋሪያ ህገ መንግስት በአንቀፅ 66 ይህ አካል የመንግስትን የህግ አውጭነት፤ የስራ አስፈፃሚነትና የቁጥጥር ተግባርን ጠቅልሎ እንደሚይዝ ይናገራል። ደርግ ደግሞ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 62 'በኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግስት ስልጣን ከፍተኛ አካል ብሄራዊ ሸንጎ ነው ይል ነበር” (ገፅ 102)

ይኸ ሁሉ ያለፈ ታሪክ ነው። ዛሬስ ይህ ”የመንግስት ስልጣን ከፍተኛ አካል” የተባለ ነገር ይት ይት ነው ያለው ?

”ዛሬ ደርግም ሶቭየቶችም የሆኑትን ሆነው” ይላሉ ዶክተር ነገደ ”ዛሬ ደርግም ሶቭየቶችም የሆኑትን ሆነው ከ ኢህአዴግ ጋር ይህንን ቲወሪ አንቀው ከቀሩት እፍኝ የማይሞሉ አገሮች መሃል የሰሜን ኮርያን ህገ መንግስት ብንጠቅስ አንቀፅ 87 'በኮርያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከፍተኛው የመንግስት ስልጣን አካል ከፍተኛው የህዝብ ምክር ቤት ነው' ብሎ ያስቀምጠዋል።” (ገፅ 103)

ደራሲው ” ይህንን ቲዎሪ አንቀው የቀሩት እፍኝ የማይሞል አገሮች ” ሲሉ በሙሉ ቢጠቅሷቸው ጊዜም ቦታም አይወስድባቸውም ነበር። እንደሚመስለኝ በመላ አለም አንድ አምስት ቢሆኑ ነው። ስም መጥራት አይሁንብኝና ቻይና፤ ሰሜን ኮርያ፤ ኩባ፤ ቪየትናምና....ኢትዮጵያ መሆናቸው ነው። ኢህአዴግም ሆነ ሌላ ማንም ዜጋ በአለም ካሉት አንድ ሁለት መቶ ያህል አገሮች መሃል እዚህ ሊስት ላይ የሚጨመሩ ሌሎችም አገሮች አሉ ካሉኝ ለመማር ዝግጁ ነኝ።

የኢህአዴግስ ህገ መንግስት ነገሩን እንዴት ነው የሚያስቀምጠው? ደራሲውን ልጥቀሳቸው፤

”ኢህአዴግ ደግሞ መጀመሪያ ከፍ ብለን እንደጠቀስነው የቡልጋሪያ ህገ መንግስት በአንቀፅ 50/2 ላይ ፌደራል መንግስቱ ' የህግ አውጭነትን፤ የስራ አስፈፃሚነትንና የዳኝነትን ስልጣን' ጠቅልሎ እንደሚይዝ ይደነግጋል። ከዚያም ቀጠል ያደርግና ይህ 'ፌዴራል መንግስት' በማን ቁጥጥር ስር እንዳለና ይህ ሁሉ ስልጣን ተጠቅልሎ የተሰጠው 'የበላይ አካል' ማን እንደሆነ ሲጠቁም የሶቭየቱን፤ የደርግንና የሰሜን ኮርያን አባባል ቃል በቃል ወስዶ በአንቀፅ 50/3 ላይ 'በኢፌዴሪ የመንግስት ስልጣን ከፍተኛ አካል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው' ብሎ ይደነግጋል።” (ገፅ 104)

ታዲያ ”የህዝብ ተመራጮች የሃገሪቱ የበላይ አካል” ተባሉና የዚህ አደጋ የት ላይ ነው? ይኸ ደግሞ ሶስተኛው ቦንብ መሆኑ ነው። ደራሲው በዚህ ጉዳይ የሚሏቸው በርካታ ነጥቦች አሉ። ስልጣን ተጠቅልሎ ለአንድ 'ከፍተኛ አካል' መሰጠቱ 'ስልጣን ያባልጋል ሙሉ ስልጣን ሙሉ በሙሉ ያባልጋል' የሚባለውን አደጋ እንዳያስከትል የስልጣን ክፍፍል መርህ ተተክሏል ብለው አያቆሙም። በሳቸው አባባል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት/የሸንጎ/የሶቭየት ወዘተ 'ከፍተኛነት' ከልኩ የሚያልፍ አይደለም። በተጨባጭ ያለው አሰራር እንዴት ነው?

" የቻይና ህገ መንግስት አንቀፅ 16 'የመንግስት ስልጣን ከፍተኛ አካል በቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ አመራር ስር የ ሚሰራው ህዝባዊ ብሄራዊ ሸንጎ ነው' ብሎ እቅጩንና የዚህን ፓርላማ የበላይነት 'ልክ' ይነግረናል" (ገፅ 105 ስርዝ የደ ራሲው)

ደርግም ሶቭየቶችም እንዳላደረጉት ሁሉ ወያኔ/ኢህአዴግም ይህንን አሰራር በህገ መንግስቱ አያሰፍረውም። ይ ህም ሆኖ ይላሉ ዶክተር ነገደ

" በተጨባጭ በያለበት ያለው ይኸው የገዥው ፓርቲ የበላይነት ነው። ትላንት መንግስቱ/ኢሰፓ፤ ዛሬ ደግሞ መለስ/ኢህአዴግ የሃገሪቱ 'የበላይ አካል' ቢሆኑ ለዚህም ራሱን የቻለ ምክንያት አለው" (ገፅ 105) በደራሲው አባባል ይ ህ እውነታ በቀጥታ ከስታሊኒስቱ የስልጣን አንድ ወጥነት ቲወሪ ጋር የተያያዘና የሱ ውጤት ነው። የስልጣን ክፍፍል ቲ ወሪ ስልጣን እኩል በሆኑ የተለያዩ ሶስት የስልጣን ዘርፎች አግድም ክፍፍል (ሆሪዞንታል ዲስትሪቡሽን ኦፍ ፓዎር) አሰ ራር ሲሆን የስልጣን አንድ ወጥነት ቲወሪ ደግሞ በአሻቅብ ውክልና (ቨርቲካል ዴሊጌሽን ኦፍ ፓወር) መርህ የሚሰራ በ ስልጣን ሳይሆን "በስራ ክፍፍል" የተመሰረተ ቲወሪ ነው። አካሄዱና ውጤቱስ?

" በአሻቅብ ውክልና መርህ መሰረት ባለ ሙሉ ስልጣን ምክር ቤት በመምረጥ ስም ስልጣን ከባለ ሙሉ ስልጣ ኑ ህዝብ ተነጥቆ ለከፍተኛው አካል ወይም ለፓርላማው ይሰጣል። ከዚህ ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን አካል ደግሞ በፓ ርላማው ውስጥ ማጆሪቲ አገኘሁ በሚል ስም አንድ ፓርቲ ወይም አንድ ድርጅት ስልጣኑን ይረከባል። ፓርቲው ደግሞ በዴሞክራሲያዊ መአከላዊነት ስም ስልጣንን ለማአከላዊ ኮሚቲው ያስረክባል። በዚሁ መርህ መሰረት ጥቂት ግለሰቦች ይህንን ሙሉ ስልጣን በፖሊት ቢሮነት እንደገና ከማእከላዊ ኮሚቴው ይረከባሉ። ከነዚህ ጥቂቶች መሃል ደግሞ አን ድ አናሳ ቡድን ወይም አንድ ግለሰብ ስልጣንን ጠቅልሎ ይረከባል። በዚህም እስከናካቴው አንድ ግለሰብ ብቻውን የሃገ ሪቱ 'የበላይ አካል' ሆኖ ቁጭ ይላል ማለት ነው" (ገፅ 106)

በዚህ መፅሃፍ ውስጥ ሁላችንም የምናማርርበት የዳኝነት ነፃነት መጥፋት፤ የገዥዎች ከህግ በላይ መሆን፤ ያለ አንዳች ተጠያቂነት የዜጎች መብት መጣስ ወዘተ እንዴት ከህገ መንግስቱ ጋር እንደተያያዘ በሰፊው ተተንትኗል። ብዙ ሰው እንደሚለው 'ይህ ህገ መንግስት የወያኔ የደደቢቱ የፖለቲካ ፕሮግራም ነው።' አወን ነው። ግን የአጋጣሚ ነገር አይደለም። በሳቸው አባባል ይህም ቀጥታ ከስታሊናዊ የህገ መንግስት ቲወሪ ጋር የተያያዘ ነው። "ፕሮግራማቲክ ፖሲ ቲቪዝም" በሚለው የሶቭየት ፅንሰ ሃሳብ መሰረት ህገ መንግስት "ህግ" መሆኑ ቀርቶ ለምንና እንዴት "የድርጊት ፕሮግ ራም" መሆን እንዳለበት ተንትነው ከደደቢቱ ሰነድ በስተጀርባ ያለውን ቲወሪ ያስረዱናል። አያይዘውም -

"ከዚህ የሶቭየት 'አስተዋፅኦ' በመነሳት አንዳንድ የህገ መንግስት ባለሙያዎች እንዲያውም በዚህ መስፈርት በ መጠቀም ህገ መንግስታትን ከሁለት ታላላቅ ጎራዎች ይከፍሏቸዋል። በአንድ በኩል ህገ መንግስት 'ህግ' አለ። በሌላ በ ኩል ደግሞ ህገ መንግስት 'ፕሮግራም' ብለው የሚጠሩት ሰነድ አለ። በቀድሞዎቹ 'ህዝባዊ ዴሞክራሲዎች'፤ በደርግ ዘ መንና ዛሬ ደግሞ በኢህአዴግ ስር ያሉት ህገ መንግስታት ከዚህኛው ጎራ የሚደመሩ ናቸው" ይሉናል። (ገፅ117)

ደራሲው በዚህ መፅሃፍ ኢህአዴግ የፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ብሎ የመሰረተው ስርአት አሁንም ልክ በስታሊኒስ ትና በስልጣን አንድ ወጥነት ቲወሪ መሰረት እንዴት ልክ በቀድሞው ሶቭየት ህብረት መልክ "ፈላጭ ቆራጭ አሃዳዊ መንግስት" እንደተቋቋመና ይህም ለሃገራችን ሰላም፤ ዴሞክራሲና አንድነት እንዴትና ለምን አደገኛ እንደሆነ አንቀፅ 3 9ን እየተነተኑ በሰፊው ያስረዳሉ። ነገሩ እንዳይንዛዛብኝና ከዶክተር ነገደ መፅሃፍ ወዲህ አሁንም አጥብቄ ከምቃወመ ው አንቀፅ 39 ይልቅ ጠቤ ከአንቀፅ 50 ጋር ስለሆነ በዚህ ዙሪያ መደረግ ስላለባቸው ነገሮች ሃሳብ በማቅረብ ይቺን መ ጣጥፍ ልቋጥር።

3ኛ የፀረ አንቀፅ 50 ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ትግል አስፈላጊነት

አንደኛ ሃሳብ። በኔ ግምት ይህ ህገ መንግስት እንዳለ ተቀይሮ አዲስ ህገ ዴሞክራሲያዊ መንግስታዊ ስርአት ያስ ፈልጋል ባይ ነኝ። በተቃዋሚዎች በኩል ህገ መንግስታዊ ስርአት የመቀየር አላማ አለ ወይ? እንደሚገባው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ህብረት /ኢዴሃህ/ በዚህ ወሳኝ ጥያቄ ግልፅ አቋም አለው። ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስታዊ ስርአት ይላ

ል። የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ በዚህ ጉዳይ ያለው አቋም ምንድን ነው? ህገ መንግስታዊ ስርአት የመቀየር አስ ላጊነት "ለማይታያቸው" ወገኖች ዶክተር ነገደ የሚሉት ግልፅ ነው፤

" ይህ ህገ መንግስት ዛሬ ለኢህአዴግ አገለገለ እንጂ ለማንም ፈላጭ ቆራጭ ዝንባሌ ላለው ገዥ ፓርቲ ሊሰራ የሚችል ሰነድ ነው። ማንም የፖለቲካ ድርጅት ፓርላማ ውስጥ ማጆሪቲ አግኝቼ በዚህ ሰነድ ላይ ተመርኩዥ አገር አስተዳድራለሁ ቢል ከወዲሁ ልንታገለው የሚገባን የዛሬ ተቃዋሚ የነገ አምባገነን አደገኛ ሃይል እንደሆነ መታወቅ አ ለበት። ለዚህ ነው ዛሬ እኛም ሆንን የሃገራችን ዴሞክራቶች በሙሉ በተቃዋሚ ጎራ ተሰልፌያለሁ የሚል ማንኛውንም ድርጅት ለመፈረጅ ይህንን አደገኛ ህገ መንግስት ከነ አደገኛ ፍልስፍናው ለመቀየር በሚደረገው ትግል በሃቅ መሳተፍ አለመሳተፉን እንደ ሁነኛ መስፈርት አርገን መውሰድ ያለብን።" (ገፅ 164)

ከዚህ አንፃር እንግዲህ የቅንጅቱ መሪዎችም ሆኑ ሌሎች በህገ መንግስታዊ ስርአት መቀየር አናምንም የሚሉ ወ ገኖቻችን በዚህ ጥያቄ ላይ ያላውቸን አቋም ግልፅ አድርገው ውይይት መከፈት ይኖርበታል የሚል ሃሳብ አቀርባለሁ።

ሁለተኛ ሃሳብና ጥያቄ። ህገ መንግስታዊ ስርአቱን ዴሞክራሲያዊ አርገን እንቀይራለን የሚሉ የህብረቱ መሪዎች ም ሆኑ ሌላው ቀርቶ አንዳንድ አንቀፅ መዘን አውጥተን....የሚሉ የቅንጅቱ መሪዎችም ቢሆኑ ማሻሻሉም ሆነ መቀየሩን እንዴት እንደሚያራምዱ ግልፅ ስትራቴጂ ያስፈልጋቸዋል። ዶ/ር ነገደ የሃገራችንን የ75 አመት "የህገ መንግስትና የም ርጫ የአልባሌነት ታሪክ" በሚለው የመፅሃፉ ክፍል እስካሁን በኢትዮጵያ ለገዥወችም ለተገዥዎችም እኩል የሚሰራ ዴሞክራሲያዊ ሰነድ ስላልታደለችበት ምክንያት ሲያስረዱ

"ሶስቱም ህገ መንግስታት ሲደነገጉ እንኳን ህብረተሰቡና ደራሲዎቻቸውም ራሳቸው ቢሆኑ ከፍ ብለን በጠቀስና ቸው እሴቶች (ማለትም ለዴሞክራሲ፤ ለህግ የበላይነት፤ ለህግ የሚገዙ ገዥዎች...) ዙሪያ አልተንቀሳቀሱም። ሶስቱም መንግስታት ለስልጣን ከተቀናቃኞቻቸው ጋር ሲተናነቁ ህዝብንም ሆነ ደጋፊዎቻውን በተለያዩ አላማዎች አሰልፈዋል። አ ፄ ሃይለስላሴ 'በዘመናዊ ስልጣኔ' ስም፤ ደርግ 'በአብዮትና በሶሻሊዝም' ስም ኢህአዴግ ደግሞ 'በሃቀኛ ሶሻሊዝምና በብ ሄሮች መብት' ስም እየተንቀሳቀሱ የስልጣን ደመኞቻውን ድል መትተዋል። እነዚህ ሃይሎች ስልጣን ሲይዙ የተንቀሳቀ ሱት ድል ያደረጉባውን አላማዎች ለማራመድ ስለነበረ ህገ መንግስታትም ለነዚህ አላማዎች መሳሪያ እንዲሆኑ አመቻ ችተው ደንግገዋል። አንድኛቸውም በዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት መሰረታዊ መርህም ሆነ ፅንሰ ሃሳብ ተንቀሳቅሰው ስ ላላንቀሳቀሱ ዴሞክራሲያዊ ሰነድ አልደነገጉም።" (ገፅ 148) ዛሬስ?

"ዛሬም ቢሆን" ይላሉ ዶክተር ነገደ "ዛሬም ቢሆን በዚህ (በዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት ጥያቄ ማለታው ነው) ዙሪያ ሳይሆን በደፈናው 'ዴሞክራሲ' 'ነፃ ገበያ ኢኮኖሚ' 'የብሄሮች እኩልነት' 'የሃገር አንድነት' ከዚያም አልፎ ተርፎ ጭፍን በሆነ 'ወያኔን ለመጣል' በሚል አላማ በሚካሄድና ይህንን ቁልፍ የዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስታዊ ስርአት ጥያ ቄ 'እንደ እንጀራ ልጅ' የሚቆጥር ግንጥል ትግል ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማምጣት አይረዳም። ስለሆነም እነዚህ ወገና ቻችን ህገ መንግስቱን እንቀይራለን ካሉ ገና ከወዲሁ በምርጫው እንቅስቃሴ ለመሳተፍ ሲነሱ በህዝባችንም በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ ፊት የኢህአዴግን ሰነድ አጋልጠውና እርቃኑን አስቀርተው በዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት ወደ ዴሞክ ራሲያዊ ስርአት ለመሸጋገር እ-ንደሚታገሉ በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል።" (ገፅ 167)

ከዚህ ተነስቼ የማቀርበው ሃሳብ ግልፅ ነው። ህብረቱም ሆነ ቅንጅቱ በጋራ ሆነው (አንዱ አሻፈረኝ ካለ ደግሞ በዚህ ሃሳብ የሚስማማው ሃይል ብቻውን) በአዲስ አበባ አንድ "ፀረ አንቀፅ 50" ሰላማዊ ሰልፍ ጠርቶ በህዝባችንም ሆነ በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ ፊት ኢትዮጵያ በመላው አለምም ሆነ በአፍሪካ ከሚነፍሰው የዴሞክራሲያዊ ለውጥ ንፋስ ተነ ጥላ ያለች አገር መሆኗን ማጋለጥና ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ለሚደረገው ትግል አዲስ እስትንፋስ ለመስጠት መንቀሳቀ ስ ያስፈልጋል። ለቀንዱ (ማለትም የነፃ ምርጫ መስፈርቶች እንዲሟሉ ለመጠየቅ መቶ ሽህ ሰው ሰልፍ ያወጣን) ለበሬ ው (ማለትም ለዴሞክራሲያዊ ስርአት እውንነት) አምስት መቶ ሽህ ሰው ሰልፍ ማውጣት አይቸግረንም።

ይህ ደግሞ በአለም አቀፍ ደረጃ መደረግ ስላለበት የዲፕሎማሲ ትግል ያመጣኛል። በኔ ግምት ወያኔን ብርክ ያ ስያዘው በዚህ ስታሊናዊ ህገ መንግስቱ ጉዳይ በአለም አቀፍ ደረጃ የመጋለጡ አደጋ ነው። ለዚህ ትግል እኔ የሚታየኝ ጥሩ የታሪክ አጋጣሚ አለ። ዛሬ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኮንዶሌሳ ራይስ የህግ ተማሪ ብቻ ሳይሆኑ ስ ልጠናቸው በሶቭየቱ አለም ላይ ያተኮረና የረሸያን ቋንቋ የዚችን ሃገር ታሪክ፤ የፖለቲካና የህግ ተቋማት ቲወሪውንም

ፕራክቲሱንም አገላብጠው የሚያውቁ ምሁር ናቸው። አዲስ አበባ በመቶ ሽህ የሚቆጠር ህዝብ "ፀረ አንቀፅ 50" ሰላማዊ ሰልፍ አደረገ ቢባል ያለ አንዳች ትርፍ ማብራሪያ የዚህ በሰሜን ኮርያ የሚቃወሙት አንቀፅ አሰራሩም፤ መዘዙም የሚገባቸው ምሁር በመሆናቸው ከመደገፍ ወደ ኋላ የሚሉ አይመስለኝም። እንዲያውም በኔ ግምት የወያኔ "ፀረ ነገደ ብርከ" ከዚህ የመጣ ይመስለኛል።

በበኩሌ ይህንን ጥሩ የታሪክ አጋጣሚ አወሳሁ እንጅ ዶክተር ነገደ " በውጭ የሚደረገው የዲፕሎማሲ ትግል ተአማኒነትና ቀጣይነት እንዲኖረው ከተፈለገ "ነፃ ምርጫ ከሚለው አልፎ ከወዲሁ ለነፃ ምርጫና ለዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት ስርአት መሆን ይኖርበታል" ሲሉ አሳማኝ መከራከሪያዎች አሏቸው።

አንደኛ አሁን እንደሚደረገው በውጭ የሚካሄደው ትግል በምርጫ ላይ ካተኮረ "የአህያ ውድቂያ" ይሆናል ባይ ናቸው።

" መጀመሪያ በዲፕሎማሲው መልክ የሚያስፈልገንን የተአማኒነት ጉዳይ እናንሳ። ትግሉ '*ላለፉት አስራ ሶስት አመታት በሃገሪቱ መድበለ ፓርቲ ስርአት መስርቼ፤ ነፃ ምርጫ እያዘጋጀሁና እያሸነፍኩ እ-ዚህ ደረስኩ*' እያለ ከሚለፍፍና በኛ ፊት ባይሆን እንኳን በውጭ አሳዳሪዎቹ ፊት ትንሽም ብትሆን ተአማኒነት ካፈራ ሃይል ጋር ነው። የህዝብ ሃብት እየረጨ በሚያሰማራው ሎቢ ብርታት በዚች መስክ ብቻ ተወስነን የምናደርገው ትግል አሸናፊው ያልለየለት 'የአህያ ውድቂያ' ሊያደርግብን ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ 'አንድና አንድ ሁለት' በሚል መልክ በሃገራችን የተተከለው ህገ መንግስት እንዴትና ለምን የሰሜን ኮርያው አይነት ስታሊናዊ ህገ መንግስት እንደሆነ ማሳየቱ የአህያ ውድቂያ አይሆንም...." (ገፅ 199)

ሁለተኛ የዲፕሎማሲው ትግል "ለነፃ ምርጫና ለዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት" በሚል መፈክርና አላማ ካልተንቀሳቀሰ የትግሉ ቀጣይነትም ችግር ይነሳል ባይ ናቸው።

" የትግላችንን አድማስ 'በነፃ ምርጫ' ጥያቄ ከወሰንነው ከግንቦት ማግስት ጀምረን እስከ ቀጣዩ ምርጫ ድረስ ' የምንለው አጥተን ' የመቀመጡና ደጋግመን እንዳስጠነቀቅነው በዲፕሎማሲውም መስክ ትግሉን 'የምርጫ ሰሞን ግርግር' የማስመሰሉ አደጋ ይኖራል።" (ገፅ 200)

እንግዲህ ጥሪየ ግልፅ ነው። ይቺን አገር ካለችበት አዝቀት ለማውጣት የአመራር ሃላፊነት የወሰዳችሁ ዜጎች ምሩን። በመሰረታዊ ጥያቄዎች ላይ ግልፅ አቋም አሳዩን። ለተግባራዊነቱም አንቀሳቅሱን፤ ሰልፍ አውጡን። ይህ ካልተደረገ ደራሲው እንዳሉት "ባልሆነ አቅጣጫ በመኳተን በእርግጥ የእኛንና የኢትዮጵያን ህዝብ ወርቃማ ጊዜ እያባከንን መሆናችን" መሰመር ይኖርበታል።

ነጋቱ ሃይሌ (ነገጸ)